# አማራ

## ***<u>የአማራ ማህበራት በታላቋ ብሪታንያ የተሰጠ ወቅታዊ መግለጫ፡፡</u>***

***በፈጣሪ አምሳል በተፈጠረ የሰው ልጅ መታረድ ላይ ቆም የፖለቲካ ቁማር መጫዎት ፍፁም አዉሬነት ነው፡፡***

የአማራ ማህበራት በእንግሊዝ በሰሜን ሸዋ ሰላሌ የተፈፀመው የሰው ልጅ መታረድ በፍፁም የሚወገዝ ድርጊት በመሆኑ ይህን ያደረገ ወይም ያስደረጉ አካላት ለፍርድ እንዲቀርቡ ለአለም አቀፍ የሰው ልጅ መብት ተሟጋጆችና ሌሎች ገለልተኛ አካላቶች  እንዲያጣሩት ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

ከድርጊቱ በተጨማሪ እጅግ ልብ የሚነካው ደግሞ የህዝብን ደህንነት የሚጠበቅበት ዙፋን/ቤተመንግሰት/ ላይ ተቀምጦ ሌላ የዘር ፍጅት ጥሪ የሚያደርገው የአብይ አህምድ ዘር ተኮር አገዛዝ መሆኑ ነው፡፡ አገዛዙ በቤተመንግሰት ተቀመጦ እንደ ኒኩለር መርዛማ ጨረሩን በመርጨትና እና ህዝብን በመከፋፈል አንድን ዘር ለይቶ የሚያጠፋ  መልዕክት በኢትዮጵያ ምድር እያስተላለፈ ይገኛል።

የጀግንነት መገለጫውን፣ የሀገር  መዳኛውን እና የአያት ቅድመ-አያቶችህን ዕሴት ፋኖነትን ጥላሸት ለመቀባት የሚንደፋደፉትን የዘመናችን ነብሰበላዎች እና ታሪክ አውዳሚዎች መግለጫ  እንቃወማለን። ለእዚህ ግልፅ ማሳያ የሚሆነው ላለፉት 6 አመታት አማራ ሲሰቀል፣ አማራ ተገድሎ እራቁቱን በመሬት ሲጎተት፣ አማራ በቤት ውስጥ ተዘግቶበት በጅምላ ሲቃጠል፣  አማራ ሲታረድ፣ አማራ በጅምላ ሲረሸን እና በግሬደር ተገፍቶ ሲቀበር፣ በአንድ የታዋቂ ሰው ሞት ከ200 በላይ አማራ በአንድ ቀን ሲያልቅ፣ ነፍሰጡር ሆዷ ተቀዶ ሆዷ ውስጥ ያለው ፅንስ በአማራነቱ ሲገደል፣ 17 ሴት ልጃገረዶች ታግተው ደብዛቸው ጠፍቶ አንዳች መግለጫ አልሰጠም፡፡ ይህ የሚያሳዬው በኢትዮጵያ ምድር የአማራን ሂዎት ከሌላው ሂዎት  ያነሰ ዋጋ  ያለው ነው በሚል መልኩ መግደሉ እንዲቀጥል የጥፋት ጥሪ አቅርቧል፡፡ በመሆኑም  የአለም አቀፍ መንግስታት የዘር ማጥፋት ድርጊት ምርመራ እንዲጀመር በአፅንኦት እንጠይቃለን፡፡

ይህንን የዘር ማጥፋት፣ የፖለቲካ እና የሀገር አፍራሽ ጥሪ እንደ DW አማሪኛ የመሳሰሉት መገናኛ ብዙሀን ግራ ቀኙን ሳይመለከቱ አራግበውታል፡፡ ይህ ድርጊታቸው እኛ በዩኬ የምንገኝ የአማራ ማህበራትን እጅግ አድርጎ እንዳሳዘነን እና በአማራ ህዝብ ላይ ለሚደርሰው ማንኛውም ጉዳት ተጠያቂ እንደሚሆኑ ለመግለፅ እንወዳለን፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ምድራዊነት እና ሰማያዊነትን በውህደት በማሳዩት እምነት እና ፍትህ የሚሰጥበትን ታላቁን የሀይማኖት ተቋም ላይ በአመራርነት ተቀምጠው የፖለቲካ ቁማር መጫወቻ እና ለሀገሪቱ የመቅሰፍት ምንጭ የሆኑ አባቶችም ይህን መርዝ ያዘለ የዘር ፍጅት ጥሪ “በማር” ለውሰው እንዳቀረቡት ተመልክተናል፡፡ በዚሁ አጋጣሚ ለሀይማኖት አባቶች የምናቀርብላቸው ጥያቄ አለን አሱም ይህ የደም ፅዋው መቼ ነው የሚሞላው? እንደ ቀደምት የሀይማኖት አባቶች በፈጣሪ ፊት ግርማ ሞገስ አግኝታችሁ ምዕመኑን ከፈጣሪ አስታርቃችሁ የመቅሰፍት ዱላውን መቼ ነው የምታስቆሙልን? የተሸከማችሁትስ መለኮታዊ ሥልጣን መቼ ነው የሚያስፈራችሁ እና ለእውነት መሰዋዕት ሆናችሁ

ለህዝባችሁ አርዕያ የምትሆኑት? በዐብይ አህመድ ሴራና ትዕዛዝ በአሩሲ ከ14 በላይ በአማራ ላይ ጭካኔ የተሞላበት አስቃቂ የጀምላ እርድ በመንግስት ተፈጽሟል፣ የዝቋላ አባቶች ተገድለዋል፣ ይህ ጀምላ እርድ ሲፈጸም የሃይማኖት አባቶችስ ዝምታ

# አማራ

ለምን? እኛ ግን እንላለን በእምነታችን ሥም በያዛችሁት እውነት ከፈጣሪ ጋር አስታርቁን እንጂ እምነታችንን ለውሸት ፕሮፓጋንዳ እያዋላችሁ አታስቀስፉን የሚል የልጅነት ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

በሰላሌ ምድር በወንድማችን ላይ የደረሰውን አሰቃቂ ድርጊት ከአማራ ህዝብ አብራክ የወጣው የህልውና ታጋይ/ፋኖ/ ጋር በማያያዝ የተገለፀበት አውድ ፍፁም ውሸት በሴራ የታጀበ እና ሆን ተብሎ የተቀናጀ እንደሆነ ማህበራችን አጣርቶ አረጋግጧል፡፡

ፋኖ ሰው ማዳንና ሀገር ከጥፋት መታደግ እንጂ ሰው ማረድ ከአባቶቹ አልወረሰም፡፡ ለአንድ አመት ተኩል ያደረገው የትግል ጉዞ ስነምግባር እና የምርኮኞች አያያዝም የሚመሰክረውም ይህኑ ነው፡፡ ወንጀሉን የፈጸዉ ወይም ያስፈፀም አካል በማረድና በማሳረድ ከፍተኛ ልምድ ያለው እንደሆነ አፈፃፀሙ ያሳውቃል፡፡ በመሆኑም ጉደዩን ገለልተኛ አካል እንዲያጣራው ጥሪያችንን ለአለም የሰው ልጅ መብታ ታጋዮች እናቀርባለን፡፡

ለአማራ ወጣትና ህዝብ የአሁኑ እንቅስቃሴ በግልፅ የሚያሳይህ አማራ የህልውና አደጋው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ ሥለሆነ ከታጋይ ወንድም/እህቶችህ ጋር ሆነህ ህልውናህን እንድታስጠብቅ ጥሪያችንን እናንስተላልፋለን፡፡

***<u>የአማራ ማህበራት በታላቋ ብሪታንያ</u>***፡፡